የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)
Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

የካቲት 1/2000

# በኢትዮጵያ መምሕራን ማህበር ላይ የተወሰደውን እርምጃ እንቃወም

የወያኔ አገዘዛዝ ኢፍትህዊ ፍርድ ቤት አንጋፋውን የኢትዮጵያ መምሕራን ማህበር በማፍረስ ዕውቅናን ለተለጣፊው ማህበር የሚሰጥ ህገ ወጥ ውሳኔ አስተላልፏል፡፡ የህጋዊ ማህበሩን ቢሮና ንብረት ሁሉ ለተለጣፊው እንዲሰጥ የወሰነው የወያኔ አገዛዝ በዚህ መንገድ አንጋፋውን ማህበር ለማፍረስ የመጨረሻውን እርምጃ ወስዷል፡፡

የወያኔ አገዛዝ በርዕዮቱም ሆነ አቋሙ ነፃ የሕዝብ ማህበራትና ተቋማትን መቆጣጠር ወይም ካልቻለ ማፍረስ በሚል የሚያምን ነውና የሠራተኛ ማህበራትን እንዳፈራረሰው ሁሉ የመምሕራንን ማህብር መቆጣጠር ሲያቅተው÷ ሊያፈርስ ሲሞክር ዓመታት አልፈዋል፡፡ ታጋይ አስተማሪዎችን ገድሏል፣አሳዷል፣ የማህበሩን መሪዎች ለዓመታት አስሮ አሰቃይቷል፡፡ በጎን ደግሞ የራሱን ተለጣፊ ማህበር በማቋቋም ሊያሰማራ ሲፍጨረጨር መቆየቱ ይታወቃል፡፡ የኢትዮጵያ መምሕራን ማህብር በመላ ሀገሪቷ የሚንቀሳቀስና በብሄረሰብ ሳይለያይ የተደራጀና የሰራ በመሆኑ ለወያኔ የማይዋጥ የእሳት አሎሎ ሆኖ ቆይቷል፡፡ አስተማሪዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዴሞክራሲ ባካሄደው ትግል ሁሉ ግንባር ቀደም ሆነው በመታገል መሥዋዕት ከፍለዋል፡፡ ማህበሩና አስተማሪዎችም በቀጥታ ከተማሪዎችና ወጣቶች ጋር የተየያዙ በመሆናቸው ወያኔ የኢትዮጵያን ወጣቶች ሊከፋፍልና ሊበታትን ሲነሳ በግድ ከኢትዮጵያ መምሕራን ማህበር ጋር መጋጨት ነበረበት፡፡ ማህበሩን ለማጥፋት የወያኔ አገዛዝ ከ 1983 ዓ.ም ጀምሮ ሲሞክር ቆይቶ በሰሞኑ ፍርደ ገምድል ውሳኔው  የመጨረሻ ጥቃቱን ለማድረስ ተነስቷል፡፡

አምባገነን ሥርዓቶች ነፃ የሕዝብ ማህበራትን ማፍረስ ልምዳቸው ነው፡፡ የወያኔ ቡድን ከደደቢት ጀምሮ ሕዝብን መቆጣጠርና ማፈን ሥራው እንደሆነ  የሚታወቅ ነው፡፡ ለሥልጣን ሲበቃም ተለጣፊዎችን ቀፍቅፏል፡፡ ነፃ ድርጅቶችን አግዷል፡፡ ነፃ የሕዝብ ድርጅቶችን በሞላ ጎደል አፍርሶ በምትኩ የራሱን ተቋሞች መስርቷል፡፡ ዛሬ በሚቆጣጠረው ፍርድ ቤት አማካኝነት የኢትዮጵያ አስተማሪዎች ማህበርን ለማፍረስ የወሰደው እርምጃ የሚወገዝና ተቃውሞ ሊደርስበትም የሚገባ ነው፡፡ በዝምታ ሊታለፍ የሚገባው ሳይሆን በሀገር ቤትም ሆነ በውጭ ማኅበራት የተቀነባባር ተቃውሞ መደረግ አለበት፡፡ በተለይ በሀገር ቤት አስተማሪዎችና ተማሪዎች በሥራ ማቆም አድማ ይህንን ህገ ወጥ የወያኔ ውሳኔ መቃወም አለባቸው፡፡ ሁሉም ሀገር ወዳድ ድርጅቶችም ይህንን ዓይነቱን የተቃውሞ ጥረት ለመደገፍ መነሳት ይኖርባቸዋል ብሎ ኢሕአፓ እያመነ አባለቱና ደጋፊዎቹም በዚሁ መልክ እንዲንቀሰቃሱ ጥሪ ያስተላልፋል፡፡

የኢትዮጵያ አሰተማሪዎች ማህበርን ከጥቃት እንከላከል!!

**EPRP**
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

**EPRP**
BP 22
Bois Colombes 92270
France

**E-mail** ESPIC@aol.com **Website:** http://www.EPRP.com